# የACPS Express 12/16/2022: ለእያንዳንዱ-ሰው፣ አስደሳች የክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) ቪዲዮ — ላላዩት-አስተላልፉ!

## ለእያንዳንዱ-ሰው፣ አስደሳች የክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break): ላላዩት-አስተላልፉ!



በዚህ የቪዲዮ ስራ-ውስጥ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች - በACPS የክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) ወቅት ሊሳተፉባቸው የሚችሉባቸውን በርካታ እንቅስቃሴዎችን የሚያሳይ ነው (ከሰኞ፣ ዲሴምበር (Dec.) 19 ቀን 2022 እስከ ሰኞ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 2 ቀን 2023 ድረስ)። ቪዲዮው፤ ስሜታዊ፣ አካላዊ እና ማህበራዊ ደህንነትን አጉልቶ-የሚያሳይ፣ እና ካለ ጥልቅ-ተሰጥዖ ያላቸው የ'ACPS' ተማሪዎች እና ሠራተኞች አስተዋጽዖ፣ ምንም ነገር ሊከናወን የማይችል-ነበር።

## የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ-የፍለጋ የዳሰሳ-ጥናት፤ በዲሴምበር (Dec.) 21 ቀን የሚያበቃ-ይሆናል



የአሌክሳንድርያ የትምህርት ቤት ቦርድ የትምህርት ቤት ስርዓታችንን ሊመራ የሚችል አዲስ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን የመፈለግ ጠንካራ የፍለጋ-ሂደትን ጀምሯል። በፍለጋው ሂደት ላይ እንደ አማካሪ-ድርጅት/consultant ሆኖ ተሳትፎውን የጀመረው የ'McPherson & Jacobson, L.L.C Executive Recruitment and Development' ሲሆን፤ ለዚህ-የስራ ድርሻ እጩዎችን የመለየት እና የመለየት ስራን በማካሄድ የትምህርት ቤት ቦርድን ያግዛል።

እስከ 11:59 p.m. EST - ዲሴምበር (Dec.) 21 ቀን 2022 ድረስ ክፍት-ሆኖ እስከሚቆየው የዳሰሳ-ጥናት አማካኝነት፣ ያላችሁን አስተያየት እንድትሰጡም እንጋብዛችኋለን። የዳሰሳ-ጥናቱ ማገናኛዎች (Links)፣ በበርካታ ቋንቋዎች መገኘት ይችላል: እንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ አረብኛ እና ዳሪ።

“በጣም ወደ ጥሩ-ውጤት የሚመራ እርምጃ እያደረግን ወደፊት እየገፋን እና ግልጽና በደንብ-የታሰበበትን ሂደት ቀርጸን - ይህም አዲሱን ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን ለመሰየም  የትምህርት ቤት ክፍላችንን/division የሚመራልን ይሆናል፤” ብለዋል የትምህርት ቤት ቦርድ - ሊቀ-መንበር ሜጋን አልደርተን (Meagan L. Alderton)። “ሁልጊዜ ግባችን የሚሆነው፣  ተማሪን-ባገናዘበ እና የመረጃ-ስብስብ ላይ ትኩረት ያድረገ (data-driven)፣ አዎንታዊ የትምህርት ባህልን መጠበቅ እና ማቆየት ነው።”

ይህ ሂደት በስራ-ላይ እየተካሄደ ባለበት ጊዜ፤ ከዚህ በታች በጊዜ-አቀማመጥነት በተቀመጠው መሰረት - ጎን-ለጎን በመሆን፤ ቋሚ የሆነ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን እስከ ማርች (March) 2023 መጨረሻ ድረስ ለመሾም ያለንን ጠንካራ ግባችንን መገንባት እና አላማችንን-ማሳካት ነው። ይህ የጊዜ-አቀማመጥ (timeline)፤ ከሠራተኞች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቡ - ትርጉም-ሰጪ አስተያየቶችን የማግኛ ዕድሎችንም ያካተተ ነው። የACPS ማህበረሰባችንን ሊመራ የሚችል የሚቀጥለውን ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅን በመምረጥ-ስራ ላይ እየተሰማራን ባለንበት-ጊዜ፤ እናንተ-የምትሰጡት አስተያየት (feedback) - የሚበረታታ እና ከግምት-ውስጥ የሚገባ ነው።

ፍላጎት-ያላቸው አካላቶች፤ የስራ-ድራሻ ዝርዝር-መግለጫውን (job description) እና የማመልከቻ ሂደቱን መመልከት ይችላሉ። እንደሁልጊዜውም፤ ለጠቅላላው የACPS ማህበረሰባችን ለሚያደርጉት ቀጣይነት ያለው እርዳታ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

**የፍለጋ የጊዜ-አቀማመጥ (Search Timeline):**
**ከዲሴምበር (Dec.) 9-21 ቀን፣ 2022**
የባለድርሻ-አካላት (Stakeholder) የዳሰሳ-ጥናቶች ይጀመራሉ

**ዲሴምበር (Dec.) 14 ቀን እና 15 ቀን፣ 2022**
ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር፣ ከማዕከላዊ ቢሮ ሠራተኞች እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ የ‘PTAC’ ቦርድ አድቫይዘሪ ኮሚቴዎች፣ የከተማው ሠራተኞች እና አመራሮች፣ የማህበረሰብ ቡድኖች እና አመራቶች ጋር ውይይቶች-ይደረጋሉ

**ጃንዋሪ (January) 2023**
የባለድርሻ-አካላት (Stakeholder) ሪፖርት ፖስት-ይደረጋል (posted)

**ፌብሩዋሪ (Feb) 2 ቀን 2023**
የማመልከቻዎች መቀበያ-ጊዜ የሚዘጋበት-ቀን

**ማርች (March) 2023**
የመጨረሻ-ተመራጭ እጩዎች ቃለ-መጠይቅ

**በማርች (March) 2023 መጨረሻ-ላይ**
አዲስ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ (superintendent) መምረጥ

**ጁላይ (July) 1 ቀን 2023**
ቋሚ የስራ-ድርሻው ይጀምራል

## የትምህርት ቤት ቦርድ 2024-33 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም (Capital Improvement Program (CIP) በጀትን ተቀብሏል



የአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤት ቦርድ፣ ሃሳብ-የቀረበውን የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)ን የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም (Capital Improvement Program (CIP) በጀት-የሆነው፣ ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት የሚዘልቀውን $457,257,200 - በዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 ስብሰባው-ላይ ተቀብሎታል። ይህ ተቀባይነት ያገኘው የCIP የበጀት ዓመት (Fiscal Year (FY) 2024-33 በጀት፤ የACPS ተቋማትን የዘመናዊነት ስራ እና የበለጠ ደህንነታቸው የተጠበቀ ለማድረግ፣ የቴክኖሎጂ ማሻሻያዎችን፣ የመጫወቻ-ሜዳዎችን የማስተካከል እና በአዲስነት የተገዛውን በ1703 N. Beauregard St. ህንፃን በመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት እንደገና-ማስተካከል ስራ ላይ ጊዜያዊ ቦታ ሆኖ ካገለገለ በኋላ ወደ አዲስ ትምህርት ቤት መቀየርን ያካተተ ነው።

“የACPS ተቋማትን እና የገንዘብ (financial) አገልግሎቶች ቡድኖችን - በዚህ የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም በጀት፣ ለአሳዩት ጠንካራ-ስራ እና ለተማሪዎቻችን ፍላጎቶች በምላሽ-ሰጪነታቸው፤ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። ይህ በጀት፣ ከተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ቤተሰቦች፣ እና የማህበረሰብ አባላቶች፣ የአሌክሳንድርያ የትምህርት ቤት ቦርድ ካዳመጠ በኋላ - ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ስራዎች ምላሽ-መመስጠት የተወሰደ-እርምጃ ነው። ለተማሪዎቻችን ተመራጭ-የሆነ ዕድሎችን በመስጠት ለስኬት እንዲበቁ የሚያስችላቸውን አስፈላጊ-የሆነ የመማሪያ አካባቢዎችን፣ እና ደህንነታቸውን እና የቀለም-ትምህርት ስኬታማነታቸው ሊደግፍ የሚችል የመገኛ-ምንጮችን ማቅረብ - ወሳኝ-የሆነ ነገር ነው፣” ብለዋል የአሌክሳንድርያ የትምህርት ቤት ቦርድ - ሊቀ-መንበር ሜጋን አልደርተን (Meagan Alderton)።

የ‘CIP’ በጀት ከ‘Combined Funds Budget’ የተለየ ነው፤ ይህም የሚከተሉትን ሦስት የተለያዩ የገንዘብ-እርዳታዎችን ያካትታሉ: የክንውን-ስራ (Operating)፤ የግራንት/Grant እና ልዩ ፕሮጀክቶች፤ እና የትምህርት ቤት የምግብ-አቅርቦት (School Nutrition) ናቸው። ስለ ACPS በጀቶች ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት፤ የACPS Budgetsን ጎብኙ።

## የዲሴምበር (December)፣ ተማሪን እና ሠራተኛን - እውቅና-መስጠት




በዚህ በአለፈው ዓመት ውስጥ - በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ በርካታ ውጤትን ያገኙባቸው ስኬቶች ነበሯቸው። የ2022 ዓመትን የምንዘጋው፣ በትምህርት ቤታችን ክፍል/division ውስጥ፣ በተደረጉ ከበርካታ እውቅና-መስጠቶች ጋር ይሆናል።

## የACPS የገንዘብ (Financial) አገልግሎቶች መምሪያ፣ ለአሳየው-የላቀ ብቃት እውቅናን-አግኝቷል

ACPS፤ በመንግስታዊ የሂሳብ-አያያዝ እና የገንዘብ ሪፖርት ማድረግ ስልት - ከፍተኛ ደረጃ ያለው እውቅና አግኝቷል። የአሜሪካ እና የካናዳ የመንግስት የገንዘብ ሹሞች ማህበር (The Government Finance Officers Association of the U.S. and Canada (GFOA)፣ ለክፍሉ/division ለበጀት ዓመት ማለቂያ ለሆነው ጁን (June) 30 ቀን 2021 - ለአሳየው ዓመታዊ አጠቃላይ የገንዘብ ሪፖርት አቀራረቡ - የላቀ-ደረጃን ያስገኘውን ሰርተፊኬትን ሸልሞታል። ልክ-እንደዚሁ፤ ACPS ላሳየው የገንዘብ ሪፖርት አቀራረቡ፣ በ'School Business Officials (ASBO)'፣ የላቀ ብቃት እውቅናን-ሰጥቶታል።

ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፤ ይህ በእርግጥም ሊያገኙት የሚገባቸው እውቅናን ለማግኘት የበቁት፣ ለዋና የገንዘብ ሹም ዶሚኒክ ተርነር (Dominic Turner) ምስጋና-እንዲደርሳቸው አስታውሰው-ነበር። "በስብሰባው ላይ፣ 'GFOA' ከፍተኛ ደረጃ የሚሰጠው ፕሮግራም፣ የACPS የገንዘብ-አያያዝ ሪፖርት የ'spirit of full disclosure'ን በግልጽነት የገንዘብ አያያዝ ታሪኩን በመግለጽ ያሳየ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ተጠቃሚ-የሆኑትን እና ተጠቃሚ ቡድኖችን ሪፖርቱን እንዲያነቡትም በማበራታታት ያገለገልም ነው፣" ብለዋል ዶ/ ኬይ-ዋየት (Dr. Kay-Wyatt)።

"የሂሳብ-አያያዝ ቡድናችን ምንም-የትኩረት ብርሃን አብዛኛውን-ጊዜ ባይሰጠውም እንኳን፣ ሁልጊዜ ከበስተጀርባ ሆኖ ተገቢ የሆነ የገንዘብ ቁጥጥር ሂደት እንዲኖር የሚሰራ ነው፣" ብለዋል ተርነር ጨምረው። "እነዚህ የእውቅና-መስጠት ሽልማቶች፤ የACPSን የውስጥ ቁጥጥሮችን እና በሪፖርት አቀራረብ ግልጽነት ላይ እየሰራ እንዲቀጥል የሚያደርግ እና፣ ለሂሳብ-ክፍላችን ቢሮ ጠንካራ-ስራ እና ትጋትን እውቅና-መስጫ ናቸው።"

የ'GFOA Certificate of Achievement'ን ማግኘት፣ ጉልህ የሆነ ስኬታማነት መገኘቱን - በመንግስት እና በአስተዳደሮቹ የሚወክልን ነው። የስኬት-የሽልማት ሰርተፊኬት (Certificate of Achievement) ለመንግስት-መስሪያ ቤት በሚሰጥ ጊዜ - የ'Financial Reporting Achievement (AFRA)' ሽልማትም ለግለሰቡ(ቦች) ወይም በመንግስት ለተወከለው መምሪያ - እንደ ቀደምት ሰርተፊኬቱን የሚቀበል ኃላፊ ሆኖ የሚሰጠውም ይሆናል።

## የ'ACPS' ሠራተኛ፣ የምስጋና-አሰጣጥ እርዳታን አቅርቧል

ባለፈው ወር ከማህበረሰብ አጋሮች፣ ከምግብ-ማከፋፈል ምንጮች እስከ በልግ የዕረፍት-ጊዜ (Fall Break) ጥቅም-ከሚያገኙ ቤተሰቦች ጋር - የACPS ትምህርት ቤት ማህበራዊ ሠራተኞች (social workers) ጋር-ግንኙነትን ባደረጉበት ጊዜ የተካሄደ ነበር። በክፍሉ/division ዙሪያ፣ 500 ምስጋና-መስጫ ቅርጫቶች፣ እና 268 የግሮሰሪ የስጦታ ካርድ (Gift Card) - ቤተሰቦቻችንን ለመርዳት ተከፋፍለዋል።

"አብዛኛዎቹ የማህበራዊ ሠራተኞቻችን - ተጨማሪ ሰዓታትን በምሽቶች ላይ እና በቅዳሜና እሁዶች ላይ በመስራት ስራው እንዲከናወን አድርገዋል፣ እና የሚገርም-ስራን ሲያከናውኑ ነበር፣" ብለዋል የትምህርት ቤት የማህበራዊ ስራ ዳይሬክተር ፋይዛ ጃክሰርን (Faiza Jackson)። በተጨማሪም፤ በማዕከላዊ ቢሮው ውስጥ ለተካሄደው ስራ ምስጋና-ይግባቸው እና፣ የቤት-አልባነት ተሞክሮ ለደረሰባቸው ቤተሰቦች የመረጃ-ምንጮችን በማስገኘት እርዳታ እንዲያገኙ ተደርጓል።

የማህበረሰብ ለገሳ-ሰጪዎች ሆነው የተካተቱት: Alexandria Free Methodist Church; Alexandria Police Department; Alfred Street Baptist Church; ALIVE! Food Bank; Assistance League of Virginia; Cameron Station; Casa Chirilagua; Communities in Schools; Elevate Church; Project Giveback; TNK/Bridge to Success; Youth for Tomorrow and Youth Uncut. በተጨማሪም፤ በትምህርት ቤት መሠረት ካደረጉ የወላጅ-አስተማሪ ማኅበሮች (Parent Teacher Associations (PTAs)፣ በርካታ እርዳታዎች መጥተው-ነበር።

ጃክሰን (Jackson) ጨምረው ሲናገሩ፤ "ይህ ጥረት፣ በርካታ ማስተባበርና ማቀናበርን የሚጠይቅ እና ለተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻችን ያለውን እንክብካቤ እና እርዳታ በጥሩ-ሁኔታ ሊያንጸባርቅ የቻለ-ግሩም ነገር ይመስለኛል።"

## ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት የአቀባበል ስነስርዓት ላይ፣ ACHS ወኪል-ሆኖ ቀርቦ-ነበር




*ፎተግራፉን-እዚህ እንድንጠቀምበት የሰጠው (Photo courtesy)፤ የከንቲባ ቢሮ ነው*

የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS)፣ በዲሴምበር (Dec.) 1 ቀን 2022 ላይ፣ በዋይት-ሃውስ (White House) ለፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ኤማኑኤል መክሮን (Emmanuel Macron) እና ለባለቤታቸው - ብሪጂት መክሮን (Brigitte Macron) በተደረገው የአቀባበል ስነስርዓት ላይ - በሚገባ-ተወክሎ ነበር። የACHS የፈረንሳይ አስተማሪ ብሪጂት ቶሚች (Bridget Tomich) ስነ-ስርዓቱን ከአስራ-ሁለተኛ ክፍል የፈረንሳይ ተማሪዎች ከሆኑት ከዲአና ኮሲንስኪ (Deanna Kosinski) እና ፍራንሲስ ፔና ኩሩዝ (Francis Peña Cruz) ጋር በመሆን፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ ከንቲማ ጀስቲን ዊልሰን (Mayor Justin Wilson) እንግዶቻቸው አድገዋቸው ተካፍለው-ነበር። “ይህን በሕይወት-አንድ ጊዜ ሊገጥም የሚችል ዕድልን፣ ከንቲባው እና የፈረንሳ አስተማሮዎቻችን ስለሰጡን፤ ከሚገባው-በላይ ደስተኞች ነን፣” ብለዋን ኮሲንስኪ (Kosinski) እና ፔና ኩርዝ (Peña Cruz)። ቶሚች (Tomich) ጨምረው-ሲናገሩ፤ “በእነዚህ ሁለት አገሮች ለረጅም ጊዜ የቆየውን ትስስር እውቅና-በሚሰጥ፣ ለእኔ-ልቤን በሚነካው በዚህ ወሳኝ ዝግጅት ላይ እንዲካፈል የስራ-ባልደረባዎቼ ስለመረጡኝ፣ ምንኛ-ክብር ነው።”

ይህ ስነ-ስርዓትን በመካፈል፣ የACHS ቡድን - ከሁለቱን ከአሜሪካ ፕሬዚዳንድ እና ከፈረንሳይ ፕሬዚዳን የተሰጡትን ንግግሮች ያዳመጡ እና፣ በፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የስራ-ዘመን የመጀመሪያ የአገር-አቀፍ ጉብኙ በሆነው ውስጥ መካፈል-ችለዋል።

## የቲታኖች፣ የ‘Swim & Dive’ ቡድን - አሸናፊነት



የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የ‘swim & dive’ ቡድን፣ የከንቲባውን ዋንጫ - የአሌክሳንድርያ የ‘Tri-City Championship’ን - የዋና-ቡድን በማሸነፍ፣ በኖቬምበር (Nov.) 30 ቀን 2022 ላይ የራሳቸው አድርገው ወስደውታል። ቲታኖች (Titans) - የሦስት-ጊዜ ሻምፒዮናዎች፤ ከተወዳዳሪዎቻቸው ከ‘Bishop Ireton High School (BI)’ እና ከ‘St. Stephen’s and St. Agnes School (SSSA)’ ጋር፣ በ‘St. James’ የስፖርት ሜዳዎች ላይ በመጫወት አሸናፊ-ሆነዋል።  የወንዶች እና የሴቶች ቡድኖቹ-ሁለቱም፣ የመጀመሪያ-ደረጃ ላይ የተቀመጡ ሲሆን፣ በፕሮግራሙ ታሪክ ውስጥ ሶስተኛውን ማዕረግ ለማግኘት በቅተዋል።

“ይህ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነው፤ ለጉራ-ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ለከተማችን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአንድላይ-ሆነው ለመዳዝም ነው፤” ብለዋል አሰልጣኝ ጆን ጉሊክሰን (Coach John Gullickson)።

የቡድኑ የውጤት-ደረጃዎች የነበሩት፤ SSSA–89, BI–240 እና ACHS–287 ነበሩ። ቲታኖች (The Titans) ብቻቸውን ያመጡት ሜዳሊያዎች 31 ናቸው: 12 ወርቅ/gold፣ ስምንት ብር/silver እና 11 መዳብ/bronze። ከስድስቱ የቅብብር ሩጫዎች (relay races) በ'medley' እና 'freestyle'፤ ቲታኖች (Titans) በአምስቱ - የመጀመሪያ ደረጃ ቦታን ወስደው አሸንፈዋል።

ጉሊክሰን (Gullickson) - በመጀመሪያ ወደ ቲታኖች የመጡት በ2018 ሲሆን፣ እንደተናገሩትም፤ ይህ ሲዝኑ (season) የመጀመሪያ-ግሩም መንገድ እና ወደ ተለመደ-ተግባር የመመለሻ-መንገድም ነው። እስከዛሬ-ድረስ፣ ቡድኑ፣ በፕሮግራም ዝግጅቶች ላይ ከ24ቱ በ14 የሬከሮችን ቦታ አግኝተው የተቆጣጠሩ ሲሆን፣ ያለፉት ቲታኖች በአሁኑ-ጊዜ ያሉትን ቲታኖች - አመለካከታቸውን በወደፊት አስቸጋሪ-ነገሮችን በመወጣት ላይ እንዲያደርጉ የታሪክ-ምልክትን ትተው-ያለፉላቸው ነው። "ስኬታችን የሚያንጸባርቀው - ከእኛ በፊት የነበሩ ቲታኖችን፣ በአሁኑ ጊዜ ያሉትን - የዓመታት ትጋትን፣ ስልጠናን፣ ጠብቆ-መቆየትን፣ ማደግን እና የከንውን-ሂደትን ነው፤" ብለው ሃሳብ ሰጥተዋል ጉሊክሰን (Gullickson)። "ደህንነቱን የጠበቀ፣ አስደሳች፣ ትምህርታዊ፣ ውድድርን ያካተተ እና የሁሉንም ባህል በማካተት - በቲታኖቻችን ከ8-12 የክፍል-ደረጃዎች ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ቲታኖች እና አቅሞቻቸውን ለማበረታታት በጣም እጥራለሁ።"

ለጉሊክሰን (Gullickson) - እነዚህ ውድድሮች፣ አብዛኛውን ጊዜ ጥቂት-የሆነ ጤናማ የሆነ የወንድማማች ጥልን የሚፈጥር የሆነበት ምክንያት፣ ታላቅ-ወንድማቸው፣ ኢቫን ስቲለስ (Evan Stiles) - የ'SSSA' አሰልጣኝ በመሆናቸው-ነው። ስቲለስ (Stiles)፤ በመሠረቱ፣ የጉሊክሰን (Gullickson) የመጀመሪያ አሰልጣኝ ነበሩ፣ እና ይህም መጨረሻ-የነበረው አሰልጣን የራሱ የሆነው የውድድር ጊዜያቶች ካጠናቀቀ በኋላ ነው። ጉሊክሰን (Gullickson) እንደተናገሩት፤ ወድማቸውን ተከትለው እርሱን ለመሆን ሁልጊዜ ይሰሩ እንደነበር እና እንደ አሰልጣኞችነታቸው ከዓመታት በፊት በ2007 - አንዳንድ ታሪካዊ የሆነ የከፍተኛ ደረጃ የፉክክር-ጊዜያቶች እንደነበራቸው ተናግረዋል። ጉሊክሰን (Gullickson) ጨምሮው-ሲናገሩ፤ ልክ እንደ የቀድሞ ቲታኖች "ወጣት እና አዲስ አባላቶቻችንን እንደሚመሩ ሁሉ - ይህም ሁሉም ተማሪዎች ከሚጠበቅባቸው በላይ ሰርተው ወደየግል ግቦቻቸው - ግቦችን በቦታው የማስቀመጥ-ሂደትን ተጠቅመው እንዲደርሱ እና በአንድላይ-ሆነው ደስታቸውን እንዲያከብሩ የሚያደርጋቸው ነው።"

## 'VHSL'፤ የባሊቦል (Volleyball) አሰልጣኝን እና ተጫዋቾችን ክብር-ሰጥቷል




ከአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) የሴቶች የባሊቦል ቡድን (girls' volleyball team) - አሰልጣኝ እና ሁለት ተጫዋቾች - ሁለቱም፣ ከቨርጅኒያ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ሊግ (Virginia High School League (VHSL) - ከፍተኛ-ክብርን አግኝተዋል። ዳኒኤሌ ቶርን (Danielle Thorne) - የ'VHSL' የዓመቱ ምርጥ አሰልጣኝ ሆነው-የተሰየሙ፣ ሚላን ሬክስ (Milan Rex) የ'VHSL' የዓመቱ ምርጥ ተጫዋች እና ክሎይ ዊልሞት (Chloe Wilmot) - ለ'Class 6' የAll-State First Team ሆነው ተሰይመዋል።

ቶርን (Thorne)፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) አሉሙነስ/alumnus፣ እና ከቲ.ሲ. ዊሊያምስ (T. C. Williams) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (አሁን ACHS ከሆነው) ከመመረቃቸው በፊት፣ የሦስት-ዓመት ዋና የባሊቦል ጀምሪ ናቸው። በ'St. Mary's' ኮሌጅ በሜሪላንድ/Maryland ውስጥ፣ በጀማሪ ዋና የባሊቦል ተጫዋጭ ሆነው ሄደው-ነበር። በሲኒየር ዓመታቸው ወቅት፤ ቶርን (Thorne) - የ'Capital Athletic Conference' የሣምንቱ ምርጥ ተጫዋች ሆነው ተሰይመው የነበረ እና፣ ለ'All-Capital Athletic Conference' ደግሞ የሁለተኛ ቡድን ሆነው

ተሰይመው-ነበር። ከኮሌጅ በኋላ፣ ቶርን (Thorne) አሰልጣኝ የሆኑ እና በአሁኑ-ጊዜ ከACHS ጋር ለአለፉት አምስት ዓመታት ቆይተዋል። ይህ ዓመት፣ ለቶርን (Thorne) እንደ የመጀመሪያ የቫሊቦች ዋና-መሪ አሰልጣን በመሆን የመጀመሪያ-ዓመታቸው ነው።

ሬክስ (Rex) - ለአለፉት አራት አመታት በ'ACHS' ውስጥ በርካታ ግሩም ሃሳቦችን ቀራጭ ሆና በጀማሪ ስኳድ (varsity squad) ውስጥ የምትታወቅ-የነበረች እና፣ አሁን በሳንታ-ባርባራ (Santa Barbara) ውስጥ በሚገኘው በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ሄዳ - በ'Division I volleyball' ውስጥ ለመጫወት-ቁርጠኝነትን የምታሳይ-ናት። በዚህ ሲዝን (This season)፤ ሬክስ (Rex) የሁል-ጊዜ መሪ ደፋቂ በመሆን፣ ከ1,000 በላይ ውጤታማ የሆኑ ነጥቦችን በማስገኘት፣ በሁለቱም በክልል እና በዲስትሪክ የዓመቱ-ምርጥ ተጫዋት ሆና ተሰይማለች።  ሬክስ (Rex) በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት በተሰማራችበት ጊዜ-ሁሉ የኦነር (honor) ተማሪም ሆና የቆየች ናት።

ዊልሞንት (Wilmot) - ለአለፉት አራት አመታት በ'ACHS' ውስጥ በጀማሪ ስኳድ (varsity squad) ውስጥ የምትታወቅ-የነበረች ግሩም-ሃሳቦችን የምታሳይ እና፣ በዱኬን ዩኒቨርስቲ (Duquesne University) ውስጥ የምትማር ሲሆን፣ በዚያም በ'Division I volleyball' ውስጥ ለመጫወት-ቁርጠኝነትን የምታሳይ-ናት። በዚህ ሲዝን (This season)፤ ዊልሞንት (Wilmot) የሁል-ጊዜ ረዳት መሪ በመሆን፣ ከ2,000 በላይ ውጤታማ የሆኑ ነጥቦችን በማስገኘት፣ በሁለቱም በክልል እና በዲስትሪክት የመጀመሪያ-ቡድኖች (First-teams) ውስጥ፣ ምርጥ ተጫዋት ሆና ተሰይማለች። ዊልሞንት (Wilmot) በከፍተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት በተሰማራችበት ጊዜ-ሁሉ የኦነር (honor) ተማሪም ሆና የቆየች ናት።

## የ'ACHS' አትሌቶች፣ የስምምነት-ደብዳቤ (Letters of Intent) ላይ ፈርመዋል

---

አምስት የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች፤ በኮሌጅ ውስጥ በስፖርቶች ለመጫወት ብሄራዊ የስምምነት-ደብዳቤያቸውን ፈርመዋል። ሁሉም አምስቱ፤ በ'NCAA Division I' ትምህርት ቤቶች የፈረሙ ሲሆን፣ ከፍተኛ-ደረጃ ያለው በኮሌጆች-መካከል የሚደረግ የአትሌቶች ደረጃን-የሚያሳይ ነው። ይህ የተሸበረቀ ክፍል የሚያሳየው፤ በርካታ የስቴት ሻምፒዮናዎችን እና የግል-ሽልማቶችን ነው። እነዚህ የ'ACHS' አትሌቶች፣ አራት የተለያዩ ስፖርቶችን - ወደ ኮሌጅ ከምርቃታቸው በኋላ በሚሸጋገሩበት ጊዜ የሚያወክሉ ይሆናል:

- ኤሊ ጉድሪች (Ellie Goodrich) — 'Old Dominion University'፣ ሶከር/soccer
- ኦሊቪአ ክሩዝ (Oliva Kruse) — 'Old Dominion University'፣ ቀዘፋ/rowing
- ኤቨሪ ሚለር (Avery Miller) — 'Longwood University'፣ ሶፍትቦል/softball
- ሚላን ሬክስ (Milan Rex) — 'University of California, Santa Barbara'፣ ቫሊቦል/volleyball
- ክሎይ ዊልሞት (Chloe Wilmot) — 'Duquesne University'፣ ቫሊቦል/volleyball

"የአትሌቲክ መምሪያ በእነዚህ አትሌቶች በጣም-ይኮራል፣" ብለዋል - የአትሌቲክስ እና የተማሪ እንቅስቃሴ ረዳት ዳይሬክተር - ፊሊክስ ትራሜል (Felix Trammell)።  "በኮርት ውስጥ እና በሜዳዎች ውስጥ ካሳዩት ውጤቶች ጎን-ለጎን በመሆን፣ እነዚህ ተማሪዎች - የአጠቃል ድምር ጂፒኤ (cumulative GPA) 4.3 ያላቸው ሲሆን፣ ይህም በመማሪያ-ክፍል ውስጥ ያላቸውን የመሪነት-ደረጃቸውን የሚያሳይ ነው። የዲስትሪክት፣ የክልል እና የስቴት ሻምፒዮናዎች ናቸው፣ እና ለ'Titan Pride' ተምሳሌቶች ናቸው!"

## የ‘ACHS W!se Gold Star’ አስተማሪዎች



አምስት የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) አስተማሪዎች፤ ለ2021-22 የ‘W!se Gold Star Award’ ለማግኘት፣ በትምህርት እገዛ (Support of Education (W!se) ውስጥ በመስራት እውቅናን-አግኝተዋል። እነዚህ አስተማሪዎች፤ ቢያንስ በአንድ ክፍል - ከ10 ወይም ከዚያ በላይ ተማሪዎች በ ‘W!se Financial Literacy Certification Test’ ላይ 90% የማለፊያ-ደረጃን በማስመዝገብ ያገኙ ናቸው:

- ሻውኔል ካርማይክል (Shawnell Carmichael)
- ዴቪድ ኮል (David Cole)
- ግሬግ ደሮጋቲስ (Greg Derogatis)
- ቪክቶሪያ ስቶዌል (Victoria Stowell)
- ቢውላ ዊሊስ-ብራን (Beulah Willis-Brown)

“በአስተማሪዎቻችን-እና በተማሪዎቻችን - በሁለቱም በዚህ ግሩም በሆነ ስኬታቸው በጣም-ኮተናል፣” ብለዋል ማይክል በርች (Michael Burch) - የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) የ‘Learning Academy 4’ ረዳት ርዕሰ መምህር። “ተማሪዎች በህይወት-ዘመን ችሎታቸው ላይ ለስኬታማነት አስፈላጊ የሆነውን የገንዘብ-አያያዝ ትምህርት ማወቃቸውን ለማረጋገጥ አስተማሪዎቻችን በሚገም-ሁኔታ መስራታቸው-በመሠራታዊነት አስፈላጊ ነው።”

‘W!se’፤ የገንዘብ-አያያዝ ትምህርት የሚገነባ፣ የንግድ እና የማህበራዊ ስራ-ፈጣሪነት የሚገነባ እና ተማሪዎች ለኮሌጅ እና ለዓለም-አቀፍ የስራ-ቦታዎች የሚያዘጋጅ - ትምህርታዊ ድርጅት ነው። የድርጅቱ በትምህርት የማሳወቂያ የሰርተፊኬት ፕሮግራም፤ ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከሚያስፈልጋቸው የገንዘብ-አያያዝ ትምህርት ጋር እገዛን የሚሰጥ እና ብቃት-ያለው የገንዘብ-አያያዝ እውቀት ያለው ለመሆን እንዲችሉ ዕድል ይሰጣል። ተማሪዎች ስለ የግል የገንዘብ-አያያዝ ከተማሩ በኋላ፣ የ‘W!se Financial Literacy Certification Test’ን በብሄራዊ-ደረጃ እውቅናን የሚሰጥ ሰርተፊኬትን ይወስዳሉ።

## የ‘ACHS’ ተማሪዎች፣ በቨርጅኒያ የ‘DECA የዲስትሪክት ደረጃ ውድድር/District Level Competition’ ተወዳድረዋል

የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - ተማሪዎች፤ በ‘DECA District Level’ ውድድር - ከዌክፊልድ (Wakefield) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ከዋሽንግተን-ሊበርቲ (Washington-Liberty) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር በተደረገው ውድድር፣ ከ19 ምድቦች ውስጥ በ17ቱ የአንደኛነት ቦታን በማግኘት ተቆጣጥረዋል። በተጨማሪም፤ 23 የሁለተኛ ደረጃ እና የሶስተኛ ደረጃ አሸናፊዎችም ነበሩ። በአጠቃላይ የመጀመሪያ-ደረጃ ምድብ-ከACHS አሸናፊዎች የሚያካትተው: Asma Adiba; Andrew Church; Alexander Cirmo; Esinam Dedoo; Karol De La Cruz Ortega; Celia Ek-Gonzalez; Malik Kunata; Finn McNabb; Safiyah Muhammad; Megan Robbert; Logan Schmauder; Sada Seman; Elbethel Seyoum; Saif Shannag; Liam Smith; Marian Vilar-Ramos; and Isaac Wessen.

ዓለም-አቀፍ የስራ-መስክ እና የሙያ/technical ተማሪ ድርጅት የሆነው ‘DECA’ - በገንዘብ-አያያዝ፣ በእንግዳ-ተቀባይነት፣ በአስተዳደር እና ማርኬቲንግ - እያደጉ-ለሚመጡ መሪዎች እና ስራ-ፈጣሪዎች ዝግጁ-የሚያደርግ ነው።

“ለሚከተሉት የ‘DECA dream’ ቡድን - እጅግ-በጣም ምስጋናችንን እናቀርባለን: ቴሪሳ ሻቪስ (Teresa Chavis)፣ አሽሊ ሞንትጎምሪ (Ashley Montgomery) እና ፐርሲል ብራክስተን (Purcell Braxton) - ለተማሪዎቻችን ይህን ስኬት እንዲመጣ ለረዱት፣” ብለዋል የ‘ACHS’ አስተማሪ እና የ‘DECA Advisor’ - ካትሪን ልዊስ (Catherine Lewis)።

የመጀመሪያ-ደረጃቸውን ይዘው የጨረሱ ተማሪዎች፣ በስቴት ውድድሮች ቦታቸውን ያረጋገጡ ሲሆን፣ ይህን በቨርጅኒያ ቢች (Virginia Beach, Va.) በሚቀጥለው ማርች (March) ወር፣ የሚካሄድ ይሆናል።

## የ‘ACHS’ ተማሪዎች፣ በ‘We the People’ ውስጥ ተወዳድረዋል




በኖርዘን ቨርጅኒያ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - ክልላዊ ውድድር ውስጥ We the People ውስጥ - በውድግሩቭ (Woodgrove) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በዲሴምበር (Dec.) 10 ቀን 2022 በተካሄደው ውድድር ውስጥ ለተሳተፉ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች፤ እንኳን-ደስ አላችሁ እንላለን። ምርጥ የሆነው የ‘Unit 4 Award’ - “How Have the Values and Principles Embodied in the Constitution Shaped American Institutions and Practices” በሚለው ውስጥ - ሽልማት ለሚከተሉት ተሰጥቷል:

- ኤርማኒ ቦከውድ (Armani Boucaud)
- ቲግራን ሲሴ (Tigran Ceesay)
- አደም ገብሩ (Adam Gebru)
- ማሊክ ኩናታ (Malik Kunata)

“በጠንካራ-ስራቸው እና በውጤታማነታቸው በጣም-ኮርቼባቸዋለሁ፣” ብለዋል የACHS አስተማሪ፣ ራአሊም ሻባዝ (RaAlim Shabazz) “We the People፣” ለተማሪዎች ትምህርት የሚሰጠው፣ በአሜሪካ የሕገ-መንግስት ዲሞክራሲ ውስጥ ያለውን ታሪክ እና መርሆዎችን ነው። በተጨማሪም በማበረታታት የሚያቀርበው፣ በተማሪዎች መካከል ያለውን የሲቪክ ብቃትን እና ኃላፊነትን ነው።

# ‘ACPS’፣ ዶ/ር ማርሲአ ጃክሰን (Dr. Marcia Jackson)ን እንደ-የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት (Student Services and Equity) ዋና ሹም አድርጎ ተቀብሏል



ዶ/ር ማርሲአ ጃክሰን (Dr. Marcia Jackson) እንደ የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት ዋና ሹም (chief of student services and equity) ሆነው - በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ፣ አዲስ የስራ-ድራሻቸውን እንደሚጀምሩ - ACPS ሲያሳውቅ ደስታ-ይሰማዋል። በዚህ የስራ-ድራሻ ውስጥ፤ ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson)፣ ለተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) ቢሮዎች፣ የተማሪ እርዳታ ቡድኖች፣ እና ለፍትሃዊ እና አማራጭ ፕሮግራሞች (Equity and Alternative Programs) - የታዳጊዎች ማቆያ (Juvenile Detention) ማዕከልን፣ የመጠለያ እንክብካቤ ፕሮግራም እና የማህበራዊ ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL)ን በሚያካትተው ውስጥ - የክፍል/division-አቀፍ አመራርነትን እና አጠቃላይ ምልከታን በማድረግ አገልግሎት-ይሰጣሉ። ከዚህ ቀደም ይዘው ከነበረ ከዋና የተማሪ አገልግሎቶች (student services) ዳይሬክተርነት፣ ወደዚህ የስራ-ድርሻ - ከዲሴምበር (Dec.) 12 ቀን 2022 ጀምሮ ሽግግር ማድረግ ጀምረዋል።

ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) እንዳሉት፤ “ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson) እንደ ቀጣዩ ዋና የተማሪ አገልግሎቶች እና የፍትሃዊነት (student services and equity) ሹም ሆነው ሲመጡ-እንኳን ደህና መጡ ለማለት አብራችሁን ተቀላልቀሉ! በዚህ ወሳኝ በሆነ የስራ-ድርሻ፤ በፍትሃዊነት፣ በጸረ-ዘረኝነት፣ እና በባህላዊ ሁሉን አካታች ተነሻሽነቶች ውስጥ አጠቃላይ-ቁጥጥር የሚያደርጉ እና፣ የተማሪን ደህንነት እና የአዕምሮ ጤና ሁኔታዎች ላይ ምላሽ ለመስጠት ስራዎችን ይመራሉ። የዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson)ን የልምዳቸውን ስፋት ለማግኘት እና የተማሪዎችን በደህንነት እና በትምህርት ለመደገፍ በሚረዳው ቁልፍ ወደሆኑ ፕሮግራሞች ቀጥተኛ የዕድገት ለውጥ እና ክንውኖችን ለማስገኘት የሚያስችለውን ችሎታቸውን ለማግኘት በመቻላችን፤ ደስተኞች-ነን።”

ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson) - ወደ ACPS በ2015 ዓም የተቀላቀሉ እና፣ በተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት-እኩልነት (Student Services and Equity) መምሪያ ውስጥ በማገልገል - በትምህርታዊ ዕድሎች ውስጥ ለACPS ተማሪዎች ያሉትን እንቅፋቶች በማስወገድ፤ በቀደምትነት - ከK-12 ትምህርት ቤት የካውንስሊንግ ዳይሬክተር በመሆን እና ከዚያም ለተማሪ አገልግሎቶች (student services) ዳይሬክተር ሆነው ሰርተዋል። ወደ ACPS ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ፤ ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson) - እንደ ከK-12 ትምህርት ቤት የካውንስሊንግ ዳይሬክተር በመሆን በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Arlington Public Schools) ውስጥ ያገለገሉ እና፣ በዋሽንግተን ዲ.ሲ ውስጥም ረዳት ርዕሰ-መምህር ሆነው ሰርተዋል። ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson) የስራ-መስክ ጉዛቸውን የጀመሩት በፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ ሜሪላንድ (Prince George’s County, Md.) ውስጥ እንደ የመጀመሪያ-ደረጃ የሂሳብ እና የሣይንስ አስተማሪ በመሆን ነው። በሜሪላን (Maryland) ውስጥም፤ በ24-ዓመት የስራ-ጊዜያቸው ውስጥ፣ እንደ የመጀመሪያ-ደረጃ እና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካውንስለር የስራ-ድራሻዎችንም ይዘው ነበር።

ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson)፣ ከሉዊዚያና ቴክ ዩኒቨርስቲ (Louisiana Tech University)፣ የባችለር ዲግሪያቸውን በሳይኮሎጂ ያገኙ ናቸው። ከጆርድ ዋሽንግተን  (George Washington) ዩኒቨርስቲ - በትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ማስተርስ ዲግሪ የያዙ እና የማስተርስ ዲግሪን - በትምህርታዊ አስተዳደር - ከትሪኒቲ ዩኒቨርስቲ (Trinity University) ያገኙ-ናቸው። ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson)፣ በትምህርታዊ አስተዳደር እና ፖሊሲ ጥናት - ከጆርጅ ዋንሽንግተን ዩኒቨርስቲ (The George Washington University) ዶክትሬታቸውን ይዘዋል።

ከK-12ኛ የትምህርት ልምዳቸው በተጨማሪም፤ ዶ/ር ጃክሰን (Dr. Jackson) - ከጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (The George Washington University) ጎን-ሆኖ የሚሰራ ፕሮፌሰር ሆኖ በመስራት - በሚቀጥለው ትውልድ የትምህርት ቤት አመራቶች እና የትምህርት ቤት ካንስለሮችን በመቅረጽ ላይ ዕድልን-አግኝተው ተሳትፈዋል።  በሕትመት-የቀረቡ ጽሁፎች ያላቸው ደረሲም ናቸው፣ እና አጭር-ታሪኮችን፣ ግጥሞችን እና ልብ-ወለዶች (novels) መፃፍ ይወዳሉ።

## አዲስ የትምህርት ቤት አመራር፤ በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት



በዚህ ጊዜ ላይ፤ የጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት (GWMS) የትምህርት ቤት አመራርን - ከአሁኑ የቀለም-ትምህርት ርዕሰ መምህር፣ ጂኔት ቪንሰን (Jeanette Vinson) የተጠባባቂ ርዕሰ-መምህር የስራ ድርሻን-በመውሰድ ተሸጋግረዋል። ከ2014 ጀምሮ በ‘GWMS’ ውስጥ ርዕሰ-መምህር ሆነው ያገለገሉት ዶ/ር ጄሲ ማዙር (Dr. Jesse Mazur)፤ ለሠራተኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች በዚህ ሣምንት መጀመሪያ ላይ በላኩት መልዕክታቸው - የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ለቅቀው-እንደሚሄዱ አሳውቀዋል።

“ዶ/ር ማዙር (Dr. Mazur) ለስምንት ዓመት በACPS ውስጥ የአገልግሎት ዘመናቸው እና በጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ ለሰጡት አመራትነት ልናመሰግናቸው-እንወዳለን፤” ብለዋል - የትምህርት ቤት አመራርነት፣ ዋና ዳይሬክተር፣ ዶ/ር ፒሬት ፊኒ (Pierrette Finney)። “ለቀለም ትምህርት የላቀ-ደረጃ እና ለተማሪ ደህንነት ትጋትን ያሳዩ የነበሩ እና የትብብርነት አሰራርን ከሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር አጋርነትን በመፍጠር ለተማሪዎች ጥቅም-ላማስገኘት በትጋት-ሰርተዋል። ‘GWMS’ን በመጪው-ዓመታት ሊጠቅም የሚችሉ፣ ዘለቄታ-ያላቸው የአሰራር ዘዴዎችን ቀርጸዋል።  በ‘GWMS’ ውስጥ ግንኙነቶችን ለመገንባት እና ጠንካራ እና አጋዥ-የሆነ የትምህርት ማህበረሰብን ለመፍጠር ስላደረጉት-ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።”

ለቤተሰቦች በላኩት መልዕክታቸው ውስጥ፣ ለትምህርት ቤት ላበረከቱት እርዳታ እና ተሳትፎአቸው- የGWMS ማህበረሰብን - ዶ/ር ማዙር (Dr. Mazur) ያመሰገኑ እና፣ በዚህ የስራ-ጊዜያቸው ውስጥ የጎላ-ትኩረት የሚስጧቸውን ነገሮች ላይ ምልከታ አድረገው፤ እንደ የተወሰኑ የማህበራዊ-ስሜታዊነት እና የተማሪዎች የመማር ፍላጎቶች ላይ በቦታ የተቀመጡትን ፕሮግራሞች እና የተነሳሽነት ጨምረው-አጉልተው-ተመልከተውል። ሰፊ-አመለካከት ያለው የትምህርት-ሰጪዎች ቡድንን መምራት በመቻላቸው፣ እና በ‘GWMS’ ውስጥ በነበራቸው ቆይታ በርካታ-የሕይወት ከፍተኛ ምዕራፎች ለውጦች ላይ ለመድረስ በመቻላቸው ኩራት እንደሚሰማቸው፤ እና ወደፊት ትምህርት ቤቱን የሚመሩትን አስተዳደሮች - ማህበረሰቡ መርዳቱን እንዲቀጥል ጠይቀዋል።

ጄኔት ቪንሰን (Jeanette Vinson) እንደ ተጠባባቂ ርዕሰ መምህር ሆነው፣ የስራ-ድራሻቸውን የሚጀምሩት በዲሴምበር (Dec.) 20 ቀን 2022 ላይ ይሆናል። በ2003 ዓም ወደ ACPS የተቀላቀሉ እና፣ በቀለም ትምህርት ርዕሰ መምህርነት በ‘GWMS’ ውስጥ ከ2016 ጀምሮ አገልግለዋል፤ ከዚህ-ቀደም ይዘውት የነበረ ይውስራ ድርሻ - የተማሪዎች ዲን (Dean) - (ከ2014-2016)፤ የአስተዳደራዊ ኢንተርን (ከ2013-2014) እና የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ (ከ2003-2013) ያለውን-ያካተተ ነው። ወደ ACPS ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ፤ ሚስ ቪንሰን (Mrs. Vinson)፣ በፕሪንስ ጆርጅ ካንቲ ሜሪላንድ (Prince George's County, Md.) ውስጥ እንደ ልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ ሆነው አገልግለው-ነበር። በልዩ ትምህርት (special education) - ከሜሪላንድ ኢንስተርን ሾር ዩኒቨርስቲ (University of Maryland Eastern Shore) የባችለር ዲግሪን የያዙ እና የማስተርስ ዲግሪን - በትምህርታዊ አስተዳደር - ከትሪኒቲ ዩኒቨርስቲ (Trinity University) የያዙ ናቸው።

ዶኒታ ሙሴ (Donita Muse) - እንደ ተጠባባቂ የስምንተኛ ክፍል የቀለም-ትምህርት ርዕሰ መምህር ሆነው፤ ሚ/ስ ቪንሰን (Vinson)ን በመተካት፣ ከዲሴምበር (Dec.) 20 ቀን 2022 ጀምሮ ይተኳቸዋል። በ2013 ዓም ወደ ACPS እንደ የሂሳብ አስተማሪ ሆነው በ‘GWMS’ ውስጥ ለማስተማር የተቀላቀሉ እና እንደ የሂሳት የትምህርት አሰጣጥ ስልጠና-ሰጪ (mathematics instructional coach) ሆነውም-አገልግለዋል። ወደ ACPS ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ፤ ሚስ ሙሴ (Ms. Muse)፣ በፌርፋክስ ካውንቲ ቨርጅኒያ (Fairfax County, Va.) ውስጥ እንደ ሂሳብ አስተማሪ ሆነው ሰርተዋል። በኮምፒውተር ሣይንስ፣ ከሜሪላንድ ኢንስተርን ሾር ዩኒቨርስቲ (University of Maryland Eastern Shore) የባችለር ዲግሪን የያዙ፣ የማስተርስ ዲግሪን ከፊኒክስ ዩኒቨርስቲ (University of Phoenix) - በስርዓተ-ትምህርት እና የትምህርት አሰጣጥ ከሂሳብ-ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ የማስተርስ ዲግሪ እና ከሎንግውድ ዩኒቨርስቲ (Longwood University) በትምህርታዊ አመራርነት - ማረጋገጫን ያገኙ-ናቸው።

ቋሚ የሆነ  ርዕሰ-መምህር የመፈለግ ስራውን፤ ACPS በፀደይ (spring) 2023 ውስጥ ይጀምራል።

## መጪው - የጄንዋሪ (January) ወር - ክንውን: የማህበረሰብ ተሣትፎ እና የቀን-መቁጠሪያ (Calendar)፣ ማስታወሻዎች




ለጄንዋሪ (January) ወር፤ ስለ የቀን-መቁጠሪያ (Calendar) ማስታወሻዎች እና ስለ መጪዎቹ የማህበረሰብ ዝግጅቶች፤ እወቁ። የACPS የማህበረሰብ ሁሉን-የሚያዳርስ (Community Outreach) ቡድን፤ በእናንተ አጎራባች-አካባቢ - መቼ እንደሚገኙ እወቁ!

**የክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break)**
ከሰኞ፣ ዲሴምበር (Dec.) 19 ቀን 2022 እስከ ጄንዋሪ (Jan.) 2 ቀን 2023 ድረስ
ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች፤ በክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) ምክንያት ዝግ-ይሆናሉ።

**ትምህርት ቤቶች እንደገና የሚከፈቱት እና ክፍለ-ጊዜዎች የሚቀጥሉት**
ማክሰኞ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 3 ቀን 2023 ነው
ከክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) ዝግ በኋላ፣ ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች ክፍለ-ጊዜያቸውን ይቀጥላሉ

**የደራሲ ንግግር/Author Talk: 'H.H. Leonards'፣ "Rosa Parks Beyond the Bus"ን ያቀርባል**
ማክሰኞ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 10 ቀን 2023 ከ6:30 -7:30 p.m. ድረስ
James M. Duncan Jr. Branch Library (2501 Commonwealth Ave)
በአሌክሳንድርያ መጽሐፍት-ቤት/The Alexandria Library ውስጥ ተቀላቀሉ እና፣ የደራሲ/author 'H.H. Leonard'ን - በቅርቡ ለንባብ በሚበቃው ኖቭላቸው "Rosa Parks Beyond the Bus: Life, Lessons, and Leadership"፣ ላይ አቀራረብ (presentation)ን - ሃሳብ-ሰጪ እና ትምህርታዊ ትውስታዎችን ከአስርት-ዓመታት በፊት - በሊኦናርድ ዋሽንግተን ዲሲ መኖሪያ-በሆነው ስጥ ፓርኮች እንግዳ-እንደነበሩ የሚተርክ-ስብስብን እወቁ።

**ሣሙዔል ተከር (Samuel Tucker) የመጀመሪያ-ደረጃ፣**
**ለወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - በቅድሚያ የተግለጹ ቀናቶች**
ሐሙስ፤ ጄንዋሪ (Jan) 12 & አርብ፤ ጄንዋሪ (Jan.) 13 ቀን 2023
የወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች - ለቤተሰቦች እና አስተማሪዎች፣ ስለ ተማሪው የማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም-ትምህርት የመማር ላይ - ስለሚያሳየው እድገት ለመወያየት፤ በጣም ጠቃሚ-የሆነ እዕድልን የሚሰጥ ነው። ለኮንፈረንሶቹ ስለመመዝገብ (sign-ups) በተመለከተ፤ እያንዳንዱ አስተማሪ - ከተማሪዎቻቸው፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ይሆናል።

**የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር (Dr. Martin Luther King Jr.) ቀንy**
ሰኞ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 16 ቀን 2023
ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች - የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ (Martin Luther King Jr.) በዓልን ምክንያት በማድረግ ዝግ ናቸው።

**የ'Alexandria Youth Speak Up'**
ሐሙስ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023፣ ከ6-8 p.m. ድረስ
George Washington Middle School Library (1005 Mount Vernon Ave.)
ሁሉም የመካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና ቤተሰቦታቸው፤ መረበሽን እና ጭንቀትን በጤናማ-ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚቻልበትን መንገዶች - ከአሌክሳንድርያ የማህበረሰብ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (Alexandria Department of Community and Human Services)፣ የአሌክሳንድርያ የአደንዛዥ-ዕፅ አለአግባብ መጠቀም መከላከያ ቅንጅት (Substance Abuse Prevention Coalition of Alexandria)፣ የአሌክሳንድርያ በጉርምስና ላይ ላሉ የእርግዝና ዘመቻ (Alexandria Campaign on Adolescent Pregnancy) እና ACPS ጋር በመሆን ውይይት ለማድረግ ተጋብዛችኋል። የማስተርጎም-አገልግሎት፤ በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በዳሪ፣ እና በስፓኒሽ ቋንቋዎች ይቀርባሉ። የልጅ-እንክብካቤ (Childcare) - በምዝገባ በhttps://bit.ly/alxyouthspeakup ላይ በመመዝገብ ወይም በ703-589-6499 በመደወል፣ መገኘት-ይችላል።

**የሁለተኛ ኢጋማሽ (Second Quarter) የመጨረሻው-ቀን**
አርብ፤ ጄንዋሪ (Jan.) 20 ቀን

**የአስተማሪ የስራ ቀን (Teacher Work Day)**
ሰኞ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 23 ቀን
የተለመደ የትምህርት ቀን ከሚኖረው - ከሣሙዔል ተከር/Samuel Tucker የመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት በስተቀረ፤ ለሌሎቹ ትምህርት ቤቶች - ለተማሪዎች ትምህርት የለም።

**የአሌክሳንድርያ ከተማ የሣይንስ ትዕይንት/Alexandria City Science Fair**
ሐሙስ፣ ጄንዋሪ (Jan.) 26 ቀን 2023፤ ከ5-9 p.m. ድረስ
Alexandria City High School - King Street Campus Cafeteria (3330 King St.)
ዓመታዊ መሣያ በሆነው በAlexandria City Science Fair ላይ - ከ200 በላይ ምርጥ እና ብሩሆች የሣይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የኢንጂነሪንግ እና የሂሳብ ብቃቶቻችንን በምናሳይበት ላይ አብራችሁን ተገኙ።

**መጪው - የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባዎች**

ሐሙስ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 5 ቀን 2023 በ6:30 p.m.

የትምህርት ቤት ቦርድ ዓመታዊ የአስተዳደራዊ ስብሰባ ይከናወናል።

ሐሙስ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 19 ቀን 2023 በ6:30 p.m.

በመደበኛነት-የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ፣ ይካሄዳል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባዎች፤ በአካል-ተገኝቶ በትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ ክፍሎች ውስጥ - በ1340 Braddock Place ውስጥ - ሌላ ማስታወቂያ-ካልተሰጠ በስተቀረ፣ ይካሄዳል። የማህበረሰብ የህዝብ አባላቶች፣ በአካል-ተገኝተው (in person) ወይም በዙም/Zoom አማካኝነት፣ መሳተፍ ይችላሉ። በስብሰባ የጊዜ-ሰሌዳ ላይ ሊኖሩ ስለሚችሉ ማንኛውም አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)፤ በSchool Board webpage ላይ እባካችሁ - ጎብኙ።

## ከተማ-አቀፍ ፕሮግራም - ተማሪዎች የACHS የቡና መሸጫ ሱቅን ያካሂዳሉ



የጠዋት አንድ-ስኒ ቡና መጠጣት፣ እንደ ቀኑን በንቃት ለመጓዝ የሚረዳ ሆኖ እንደሚያገለግል የሚካድ-አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታ፤ የ'Kick!' የቡና ሱቅ - በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ - ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች (students with disabilities) በከተማ-አቀፍ ፕሮግራም ውስጥ - ችሎታቸውን በማዳበር፣ በስራ-ላይ በመሆን ልምድ የሚያገኙበትን - ከፍ-ከፍ የሚያደርግ ዕድሎችን ይሰጣል። የቡና መሸጫ ሱቁ፤ በስራ-መስክ ዝግጅት ክፍላቸው በሆነው በቀኑ የመጀመሪያው ክፍለጊዜ አንዱ አካል የሆነ፣ እና ካፌ ለማስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ ይዘቶች በሙሉ ተማሪዎች እንዲማሩ እና እንዲያካሂዱ ይረዳቸዋል።

የስራ-መስክ ዝግጅት አስተማሪ የሆኑት ሳሊ ሽናይደር (Sally Schneider) እንዳሉት፤ ተማሪዎች ሁሉም የሚጠጡ-ነገሮች ማዘጋጀት እና የመስሪያ-ጣቢያቸውን ለቀዝቃዛ እና ለሙቅ መጠጦች - አይስ ቲ (iced tea)፣ ለመኔድ (lemonade)፣ ሆት ቸኮሌት (hot chocolate) እና በርግጥ-ደግሞ ቡና - ለማዘጋጀት እንዲረዳቸው ያመቻቻሉ፤ ብለዋል። ተማሪዎች በተጨማሪም፤ በፊለ-ፊት መቀበያ ላይ፣ ሄደው-የሚሰጡትን/deliveries በመስጠት፣ በማጽዳት እና በሱቁ-ውስጥ ያሉትን ዝርዝሮች (inventory) በመከታተልም ይሰራሉ። ሽናይደር (Schneider) ጨምረው-ሲናገሩ፤ በዚህ ዓመት - ፕሮግራሙ ከጠቅላላ-ትምህርት ተማሪዎች ክፍል ጋር በመሆን፣ በማስተካከል እና ሄደው-በሚሰጡ/deliveries ትዕዛዞች ለመርዳት - በቡድኑ ውስጥ ተሳትፈዋል።

"ተማሪዎች በቡና መሸጫ ሱቁ ውስጥ በመስራታቸው ይማራሉ-ብለው ብለን የምንገምታቸው በርካታ ችሎታዎች አሉ፤" ብለው ሽናይደር (Schneider) ገልጸዋል። ሽናይደር (Schneider) እንዳሉት፤ ተማሪዎች ይህን ዕድል ተጠቅመው ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር በትምህርት የማያገኙትን የልምምድ ችሎታዎችን ለማዳበር የእርስ-በርስ ግንኙነት እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣቸዋል። "ዐይን-ለዐይን በመመልከት መነጋገር/making eye contactን ለመለማመድ፣ ትዕዛዛትን በአነስተኛ ማበረታቻዎች መከተል፣ ስራን ማጠናቀቅ፣ ደንበኞችን ሰላም ማለት እና ትዕዛዛቸውን መቀበልን ይለማመዳሉ።" ከዚሁ ጋር በመሆን ደግሞ፤ ሌላ ከፍተኛ ችሎታ የሆነውን የሚጠጡ-የቡና ዓይነቶችን የመስራት እና የማጽዳት ችሎታቸውን ያዳብራሉ። ይህ የሙያተኛ ችሎታዎችን ማዳበራቸው፤ በማህበረሰቡ ውስጥ - ወደ ስራ-መስክ ለመሸጋገር ይረዳቸዋል።

“ማህበርሰብ በጉዳተኝነት ላይ ትኩረት የመስጠት-ሁኔታ ሊኖረው ይችላል፤ እኛ ግን በችሎታዎች ላይ ትኩረት እንሰጣለን፤” ብለዋል ሽናይደር (Schneider) በመጨመር - ተማሪዎች በእጃቸው የሚሰሩት ተሞክሮዎች በሚያከናውኑ ጊዜ ደስታ-ይሰማቸዋል። እያንዳንዱ ተማሪ፤ በሱቁ ውስጥ በሚከናወኑ በሁሉም የስራ-መስኮች ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን፣ ይህም ያልተመቻቸ ስሜት የሚፈጥርባቸውን ነገሮች ለመጋፈጥ እና ያላቸዋን አቅም-ለማሳየት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። “በሚሰሩት እያንዳንዱ ቡና እና በሚያቀቡበት ጊዜ፤ በራስ-መተማመናቸው ሲገነቡ ማየት ትችላላሁ።”

‘The Kick!’ ከቡና ሱቅነት የበለጠ ሁኔታ አለው፤ ይህም - አጋር ተማሪ ጓደኞቻቸው ምን ያህል ማድረግ እንደሚችሉ መመልከት መቻል እና ባላቸው ጉዳተኝነት ላይ ትኩረት ሳያደርጉ ሊያከናውኑ የሚችሉትን፤ በአጠቃላይ የትምህርት አቀማመጥ ውስጥ ያሉ ተማሪ ሠራተኛ ሆነው የሁሉንም ሕይወት የሚያበለጽ ዕድሎችን የሚሰጣቸውም ነው። “በእኔ ክፍል ውስጥ እንደ እኩያ-መካሪ (peer mentor) ሆኖ መስራት የመረጡ ተማሪዎች አሉኝ፤ ይህንን ያደረጉት በተማሪዎች ማህበረሰብ ውስጥ አንዱ-አካል መሆን ስለፈለጉ ነው፤” ብለዋል ሽናይደር (Schneider)። ለሽናይደር (Schneider) - ተሞክሮው የእርስ-በርስ ስሜትን ከፍ-ከፍ የሚያደርግ ነው። “ከእነዚህ የተማሪዎች ቡድን ጋር ለመስራት፣ ያላቸውን መልካም-ልቦች ለማየት፣ የሚያሳዩትን ዕድገት ለማየት በመቻላችን፤ ቃላቶች-ሊገልጸው አይችልም።”

‘The Kick!’፣ ከሰኞ እስከ ሐሙስ - ከ9-9:45 a.m. ድረስ ክፍት-ነው። የደንቦችን መስኮት ከኦዲተርየሙ (auditorium) አጠገብ ለሆኑት - የማድረስ/Deliveries አገልግሎቶች በACHS - King Street ቦታ ውስጥ የሚሰጡም ናቸው። ትዕዛዞች/Orders፤ በኦንላይን መደረግ-ይችላሉ። ከሺያጭ የሚገኘው ገቢ፤ ለግብዓት መግዣ እና ቡና ሱቁ ጥገና ይውላል።

## ACPS፣ የCOVID-19 ምርመራ-የማድረግ አማራጮች በመስጠት የሚቀጥል-ይሆናል




በአሌክሳንድርያ ውስጥ የሚገኙ ከሁሉም የኩራቲቭ (Curative) የCOVID-19 የምርመራ ጋር የሚገኙ ቦታዎች - በዲሴምበር (Dec.) 26 ቀን 2022 ላይ በቋሚነት የሚዘጉ ይሆናል፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ቤተሰቦች፤ አማራጭ-የምርመራ ቦታዎችን በማወቅ-መገንዘብ ያስፈልጋቸዋል።

በአጋር ድርጅታችን በሆነው በ‘Aegis’ አማካኝነት፤ ምልክት-ላላቸው ተማሪዎች እና ሠራተኞች፤ በትምህርት ቤት መሠራት ያደረገ የክትትል-ምርመራን በየሣምንቱ - ACPS መስጠቱን ይቀጥላል። ሆኖም ግን፣ በክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) ወቅት ምንም-የክትትል ምርመራ አይኖርም። ለዚህ ምርመራ እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል በ[’on-site COVID-19’ የምርመራ፣ ድህረ-ገጻችን] ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም፤ የ‘ራፒድ የምርመራ ጥቅሎች (rapid test kits)’ - ለተማሪዎች እና ሠራተኞች ከACPS የትምህርት ቤት ነርሶች ማግኘት-የሚቀጥል ይሆናል። እነዚህ የCOVID-19 ምርመራዎች፤ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ የሚደረጉ እና በትምህርት ቤት ነርሶች የሚደረግ አይደለም።

የአሌክሳንድርያ ከተማ በተጨማሪም፣ ተጨማሪ መረጃዎችን በ[ለCOVID-19 የት ምርመራ-ማግኘት ይቻላል] ላይ እንዲገኙ አድርጓል። የCOVID-19 ምርመራዎች፣ በበርካታ የጤና እንክብካቤ ክሊኒኮች ቦታዎች ውስጥ መገኘታቸው የሚቀጥል ሲሆን፣ ይህን የ‘PCR’ እና የ‘rapid antigen testing’ን ማድረግን የሚቀጥሉ ሲሆን፤ ሆኖም-ግን አብዛኛዎቹ በአካል-ተገኝቶ ወይም በርቀት ሐኪማቸውን ማየት

ሊያስፈልጋቸው ይችላል። የCOVID-19 - የ'PCR' እና የ'rapid antigen testing'፤ በበርካታ ፋርማሲዎች፣ የአርጀን ኬር (urgent care) ማዕከላት እና በ'CVS Minute Clinic' ቦታዎች ውስጥ መገኘት የሚችሉም-ይሆናል።

በተጨማሪም፤ ቫይረሱ-አንዳለ (positive) የCOVID-19 የምርመራ-ውጤቶች ያላቸው ተማሪዎች ቤተሰቦች፤ ይህንኑ ለሚከተሉት ሪፖርት ቢያደርጉ የሚጠቅም-ይሆናል: reportingcovid@acps.k12.va.us ወይም በcontacttracing@acps.k12.va.us ማነጋገር-ቢችሉ ጠቃሚ-ይሆናል። ይህን መረጃ-በማጋራት፤ የCOVID-19 ብከለት-ደረጃዎችን በትምህርት ቤት ክፍል/division ውስጥ ለመከታተል እና የአጠቃላይ የማህበረሰባችንን ጤና ለመጠበቅ ይረዳል።

## የACPS Express፣ ከክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) በኋላ ተመልሶ-ይቀጥላል




ሁሉም በየአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)  ውስጥ-ያሉ ትምህርት ቤቶች፤ ከሰኞ ዲሴምበር (Dec.) 19 ቀን 2022 ጀምሮ ዝግ-የሚሆኑ እና፤ ከሐሙስ ዲሴምበር (Dec.) 22 ቀን 2022 ጀምሮ ደግሞ የACPS ቢሮዎች - በክረምት የዕረፍት-ጊዜ (Winter Break) ምክንያት ዝግ-ይሆናሉ። ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች፤ ማክሰኞ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 3 ቀን 2023 - ተመልሰው የሚከፈቱ-ይሆናል።

በዚህም-ምክንያት፣ የሚቀጥለው የACPS Express - አርብ፣ ጃንዋሪ (Jan.) 6 ቀን 2023 ላይ የሚቀርብ-ይሆናል። ስንመለስ፤ በጣም-በቅርብ ጊዜ ስለሚገኙ የትምህርት ቤታችንን ክፍል/Division - መረጃዎችን ለማጋራት-በጉጉት እንጠባበቃለን። ግሩም የሆነ፣ አዲስ-ዓመትን እንመኝላችኋለን!

## የክረምት የአየር-ጠባይ ውሳኔዎችን፤ ACPS እንዴት እንደሚያደርግ እና እንዴት ከእናንተ ጋር እንደሚያጋራ



ወደ ክረምት ወራቶች እየገባን ባለንበት ጊዜ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (ACPS) - በአካል ተገኝቶ (In-Person) ትምህርት አሰጣጥ ሊካሄድባቸው በማይቻልባቸው ቀናቶች ላይ ዕቅድ አቅዷል። ዕቅዳችንም የሚያካትተው፤ የክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ሁኔታዎች በሚከሰቱ ጊዜ፤ የማስታወቂያ ሂደቶችን እና የመማር ሂደት መቀጠልን አካትቶ-የያዘ ነው። ግባችን፣ ማንኛውም የወደፊት ትምህርት ቤቶች መዘጋት በሚያስፈልጋቸው ቀናቶችን ጠብቀን እያለን፣ የመማር ሂደቱ እንዲቀጥል ማገዝ ነው። በክረምት የአየር ጠባይ ምክንያት - የተዘጋው የመጀመሪያው የትምህርት ቀን በርቀት (virtual) መደበኛ-ባልሆነ መንገድ (asynchronous) የሚሰጥ የትምህርት-አሰጣጥ ሊሆን እንደሚችል፤ ይህም ተማሪዎች አንድ-ዓይነት የሆነውን ማቴሪያል መማር የሚያስችላቸው ሲሆን፣ ነገር ግን -

በተለየ ጊዜያቶች እና ቦታዎች ላይ - በቀጥታ-ከሚሰጥ የትምህርት አሰጣጥ ውጪ በሆኑ መልኩ የሚሰጥበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል - ቤተሰቦች፣ ዝግጅት-ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ትምህርት ቤቶች ከአንድ-ቀን በላይ መዘጋት-የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፤ ተጨማሪ መረጃዎችን የምናጋራችሁ ይሆናል። ተማሪዎች መደበኛ-ባልሆነ መንገድ (asynchronous) ትምህርት በርቀት (virtual) መማር ውስጥ በእያንዳንዱ የትምህርት ቤት ደረጃ ውስጥ እንዴት መካፈል እንደሚችሉ ተጨማሪ-ዝርዝሮችን ለማግኘት፤ እባካችሁ የእኛን [የክረምት (winter) የአየር-ጠባይ ግንኙነቶች ድህረ-ገጻችንን] ጎብኙ።

## የክረምት-ወቅት የአየር-ጠባይ ሁኔታዎችን - መገምገም

የክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) በሚከሰት-ጊዜ፤ — እንደ በረዶ፣ አይስ/ice ወይም ከመጠን በላይ ቀዝቃዛ የአየር-ጠባይ— በሚከሰት-ጊዜ፣ እና አውቶቡሶችም ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት በደህንነት የመንቀሳቀስ ሁኔታ ሳይኖራቸው ሲቀር፤ ACPS የትምህርት ቤት ህንፃዎችን መዝጋት የሚያስፈልገው እና የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥም በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት በመኖሪያ ቤት ውስጥ ይካሄዳል። በተጨማሪም፤ ወደ ትምህርት ቤት በእግራቸው ለሚመጡ - ወደ ትምህርት ቤት መምጣቱ ደህንነታቸው-ሊጠብቅ የማይችል ከሆነ፤ ወይም ለሠራተኞች ለመጓጓዝ አደገኛ ከሆነ፤ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ የሚሰጥ የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ ለማካሄድ ውሳኔ ይደረግ-ይሆናል። በክረምት የአየር-ጠባይ (winter weather) ሁኔታዎች ወቅት ትምህርት ቤቶችን ለመዝጋት ስንመለከት፣ የተማሪዎቻችንን እና የሠራተኞቻችንን የደህንነት ሁኔታ፣ የእኛ ቁጥር አንድ ቅድሚያ የምንሰጠው-ጉዳይ ነው። ስለ መንገድ ሁኔታዎች ከአሌክሳንድርያ ከተማ የአስቸኳይ ጊዜ ቁጥጥር ሰራተኞች ጋር በመሆን፤ የመንገዶችን ሁኔታ እና የሕዝብ በእግር-መሄጃች ሁኔታዎቻቸውን ለመገምገም፤ የትምህርት ቤት ሠራተኞችም - የአውቶቡስ የመጓጓዣ መስመሮችን ደህንነት፣ የACPS የመኪና ማቆሚያዎች እና የአውቶቡስ መስመሮች በተመለከተ ግምገማ-በማድረግ ላይ፣ በጥምረት እንሰራለን።

ቤተሰቦች እና ሠራተኞች ቀደም-በልው ዝግጅቶችን ማድረግ እንዳለባቸው በማሰብ፤ ACPS፣ የትምህርት ቤት መዘጋት ውሳኔዎችን ከክረምት የአየር-ጠባይ ሁኔታው ከሚኖርበት ቀን በፊት ባለው ምሽት ለማሳወቅ ሙከራ ያደርጋል። ሆኖም ግን፤ በአየር-ጠባይ ትንበያ ዙሪያ በሚኖሩ በርካታ የማይታወቁ-ነገሮች ምክንያት፤ የመጨረሻውን የጠዋት ትንበያውን እና የመንገድ ሁኔታዎች አዲስና ማሻሻያ (update)ን ከአሌክሳንድርያ ከተማ የአስቸኳይ-ጊዜ ቁጥጥር (City of Alexandria emergency management) ሠራተኞች እስከሚሰጠን እንጠብቃለን። ሊፈጠር በሚችለው የአየር-ጠባይ ሁኔታ ቀድሞ ባለው ምሽት ውሳኔውን ለማሳወቅ በማንችል ጊዜ፤ ጠቅላይ ስራ አስኪያጁ - የትምህርት ቤት ህንፃዎች መዘጋት አለመዘጋት ውሳኔውን እና በመኖሪያ ቤት የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ ለተማሪዎች መሰጠቱን፣ በግምት ወደ 5:00 a.m. ላይ ያሳውቃሉ። በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን፤ በACPS ድህረ-ገጽ እና ‘ParentSquare’ አማካኝነት፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች መደበኛ አዲስና ማሻሻያዎች (updates)ን ያገኛሉ።

## ለ‘በመኖሪያ-ቤት የርቀት (Virtual) የትምህርት አሰጣጥ’ መዘጋጀት

በክረምት የአየር-ጠባይ ወቅት (winter weather season) እንደመደበኛ ልምድ-ሆኖ መደረግ ያለበት፤ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ፣ ተማሪዎች ኮምፒውተሮቻቸውን/ዲቫይሶቻቸውን (computers/devices) እና የመማሪያ ቁሳቁሶቻቸውን ወደ መኖሪያ ቤታቸው እንዲወስዱ በእጅጉ-ይመከራሉ። ይህ፤ በመጥፎ የአየር-ጠባይ (inclement weather) ምክንያት ትምህርት ቤቶች መዘጋት ሲኖርባቸው፤ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸው ቁሳቁሶች በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው። የመጀመሪያው የርቀት (virtual) መማር ቀን፣ በመደበኛ-ባልሆነ የትምህርት አሰጣጥ (asynchronous) በኦንላይን-የሚከናወን ሲሆን፤ ይህም፣ ተማሪዎች አንድ-ዓይነት ይዘቶች/materialን ለመማር፣ ነገር ግን - የቀጥታ (live) የትምህርት አሰጣጥ ሳይኖር - በተለያየ ጊዜያቶች እና ቦታዎች ላይ በመሆን፣ [በክረምት የአየር-ጠባይ/winter weather የግንኙነቶች ድህረ-ገጻችን] ላይ በተገለጸው-መሠረት እንዲማሩ የሚያደርጋቸው ነው። ትምህርት ቤቱ በአካል ተገኝቶ (In-Person) ትምህርት ለመስጠት ከአንድ ቀን-በላይ የሚዘጋ ከሆነ፣ ስለ ርቀት (virtual) ትምህርት አቀማመጥ - ለቀጣዮቹ ቀናቶች የሚኖረውን አዲስና-ማሻሻያ (update)፣ ቤተሰቦችን የሚያገኙ-ይሆናል።

## ከቤተሰቦች እና ሠራተኞች ጋር የሚደረግ ግንኙነት

ከክረምት የአየር-ጠባይ ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤት በሚዘጋ-ጊዜ፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች - በኢሜል እና በ‘ParentSquare’ አማካኝነት፣ ማስታወቂያን ያገኛሉ። ይህ መረጃ፤ መደበኛ የክንውን-እንቅስቃሲው እስከሚቀጥል ድረስ - እንደተለጠፈ (post እንደተደረገ) ይቀጥላል። በተጨማሪም፤ የACPS ድህረ-ገጽ፣ አጣዳፊ መስመር (hotline) እና የማህበራዊ ሚዲያ (social media) አውታሮች፤

ተገቢ-የሆነውን የመረጃ ማንቂያ (alert) የሚያካትቱ፤ እና ‘ACPS’ም፣ ከክረምት የአየር-ጠባይ ጋር የተያያዙ መዘጋቶችን በአካባቢው የዜና ማሰራጫዎች እና በማህበረሰብ አጋርነት-አማካኝነት የከትምህርት በኋላ የትምህርት-አሰጣጥን በሚሰጡ እና/ወይ በልጅ-እንክብካቤ (Child Care) በኩል፤ መረጃውን ያጋራል። የACPS ትምህርት ቤቶች ዝግ-ሲሆኑ፤ የከትምህርት በኋላ (after-school) እና የልጅ-እንክብካቤ ሰጪዎች (childcare providers) ጋር ስለ የስራ-ክንውናቸው - አንዳንድ አገልግሎት-ሰጪዎች ከተለመደው የትምህርት ቤት ቦታ ውጪ አገልግሎቶችን ሊሰጥ ስለሚችሉ፤ ከእነርሱ-ጋር በቀጥታ ያለውን-ሁኔታ እንዲያረጋግጡ ለቤተሰቦች እናበረታታለን። ሁሉም የ‘ACPS’ ሠራተኛ እና ቤተሰቦች የክረትም የአየር-ጠባይ ማስታወቂያዎችን እና አዲስና ማሻሻያዎች (updates) ወዲያውኑ ከትምህርት ቤቱ ክፍሉ/division እንደተላኩ ለማግኘት እንዲችሉ [የ‘ParentSquare አፕ/app’ን ዳውንሎድ] እንዲያደርጉ እንመክራለን።

## የክረምት የአየር-ጠባይ - ጤናማነት፤ ለACPS ቤተሰቦች



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎቶች ዳይሬክተር - ሮቢን ዋሊን (Robin Wallin) ሪፖርት-ባደረጉት መሠረት፤ በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ በጉንፋን፣ የመተንፈሻ ቫይረሶች፣ እና በኢንፍሉዌንዛ (influenza (“flu”) ሕመም-የታመሙ - ተማሪዎች እና ሠራተኞች ቁጥር መጨመሩን እየተመለከትን ነው።

በዚህ ፍሉ (flu)-መሰል በሽታ የታመሙ ልጆች፤ ሣል እና የመተንፈሻ-አካል መተፋፈን (congestion) ያላቸው፣ እና ትኩሣት፣ ብርድ-ብርድ ማለት፣ የጉሮሮ ቁስለት፣ ራስ-ምታት፣ የሰውነት-መቆረጣጠም፣ እና ድካም-መሰማት ሊኖራቸው-ይችላል። በተጨማሪም፤ በበዓላት ጊዜ ወቅት፣ የበለጠ-ጊዜ በቤት ውስጥ (indoors) በማሳለፍ - የእነዚህ ቫይረሶች መተላለፊያ-የአደጋ መጠን ከፍ-ያደርገዋል። ከበዓላት-በኋላ ወደ ትምህርት ቤት በመመለስ ጊዜ፣ የCOVID-19 ምርመራን-ማድረግ፤ የCOVID-19ን በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ መዛመትን ለመከላከል ሊረዳ-ይችላል። ቤተሰቦች፤ እነዚህን ማንኛቸውንም-ዓይነት ምልክቶች ልጃቸው ያለው ከሆነ፤  ልጁን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይልኩ በትህትና-ይጠየቃሉ። በትምህርት ቤት ውስጥ - ማንኛውም ትኩሳት ያለው ልጅ - ተሽሎት ወደ ትምህርት ቤት እስከሚመለስ ድረስ፤ በመኖሪያ ቤቱ እንዲያርፍ እና እንዲሻለው የሚላክ-ይሆናል።

በማህበረሰባችን ውስጥ፣ የCOVID-19 ቫይረስ መዘዋወር፤ እየቀጠለ የሚኖርም-ይሆናል። ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሠራተኞች፤ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሳቸው በፊት - ከህመም-የተነሳ [ማንኛውንም ምልክቶች] የሚያሳዩ-ከሆነ፤ የCOVID-19 ምርመራን እንዲያደርጉ በእጅጉ-እናበረታታለን። ነፃ የ‘rapid COVID-19’ የምርመራ-ጥቅሎች/test kits፤ ለሁሉም የACPS ቤተሰቦች፣ ከትምህርት ቤት ነርሶች ማግኘት ይቻላል።

ለCOVID-19 ቫይረሱ-እንዳለ (positive) እንደሆነ ተማሪዎ የምርመራ-ውጤቱ የሚያሳይ ከሆነ፤ እባካችሁ - ይህንኑ ውወደ የትምህርት-ገበታ መገኘት ቢሮ (school attendance office) እና፣ ወደ reportingcovid@acps.k12.va.us ኢሜል በማድረግ አሳውቁ። እባካችሁ የሚከተሉትን አስታውሱ:

- ለCOVID-19 በምርመራ ውጤታቸው ቫይረሱ እንዳለ (positive) የሆኑ ግለሰቦች፤ አስፈላጊ-በሆኑት በአምስት-ቀን የመገለያ-ወቅት (isolation period) በሆኑት-ጊዜያት - በትምህርት ቤት ውስጥ ተገኝተው መማር የለባቸውም።
- ተማሪዎች፤ ምልክቶቹ እስከተሻሻሉ-ድረስ እና ለ24 ሰዓታት ምንም የትኩሳት መቀነሻ መድኃኒት ሳይወስድ - ከትኩሳት-ነፃ ሆነው የቆዩ ከሆነ፤ በስድስተኛው ቀን ወደ ትምህርት ቤት ሊመለሱ-ይችላሉ። ከ6-10ኛው ቀን ድረስ፣ ጠበቅ-ብሎ በደንብ የሚይዝ የፊት መሸፈኛ (mask)ን እንዲያደርጉ-ይጠየቃሉ።

- ተጨማሪ-መረጃዎች - ስለ [የ‘ACPS’ የCOVID-19 መመሪያዎች፤ በኦንላይን-ላይ መገኘት-ይችላል]።

ከተለመዱ የክረምት ህመሞች-እራሳችሁን እና ሌሎችን ለመጠበቅ፤ የሚከተሉት እርምጃዎችን መከተል የሚመከር-ነው:

- ጥሩ የንፅህና-አጠባበቅን፣ ማበረታታት
    - እጆችን በሣሙና እና በውሃ በተደጋጋሚ ማጠብ፤ እና ቢያንስ ለ20 ሰከንዶች - በተለይ-ደግሞ ከታመመ ሰው አካባቢው ከቆያችሁ-በኋላ - መታጠብ።
    - በምታስሉ ወይም በምታስነጥሱ ጊዜ፤ የመጠራረጊያ-ወረቀት (tissue)ን መጠቀም፤ ወይም የክንዳችሁን የላይኛውን-ክፍል - አፋችሁን እና አፍንጫችሁን ለመሸፈን-ተጠቀሙ፤ ነገር-ግን እጆቻችሁን-አትጠቀሙ። የመጠራረጊያ-ወረቀቶቹ (tissues)ን ጣሉ፣ እና እጆቻችሁን ታጠቡ።
- የሕመሙን ስርጭት መቀነስ
    - ከታመሙ-ሰዎች ጋር የቅርብ-ንክኪ ያለው (close contact)–አይኑራችሁ።
    - የታመሙ-ሰዎች፤ ከትምህርት ቤት፣ ከስራ፣ ከትምህርት-በኋላ (after-school) እንቅስቃሴዎች፣ እና ጉዳዮችን ለማስፈጸም-ከቦታ-ቦታ መሄድ (running errands) ከማድረግ-መቆጠብ እና በመኖሪያ ቤት መቆየት አለባቸው።
    - የታመሙ ተማሪዎች ወይም ሠራተኞች፤ ለሙሉ 24 ሰዓታት - ማንኛውም የትኩሣት-መቀነሻ መድሃኒቶችን ሳይወስዱ፣ ከትኩሣት-ነፃ እስከሚሆኑ ድረስ፤ በመኖሪያ-ቤታቸው ውስጥ መቆየት-አለባቸው።
- ክትባት ተወጉ
    - የጉንፋን/flu ክትባትን እና የCOVID-19 ቡስተሮችን/boosters፤ ለቤተሰብዎ ከከፋ የመታመም-አደጋ ሊያደርሰው የሚችለውን አደጋ ለመቀመስ - ከግምት-ውስጥ ማስገባት
    - የጉንፋን/flu ክትባትን እና የCOVID-19 ክትባቶች፤ በበርካታ ፋርማሲዎች፣ ግሮሰሪ ሱቆች፣ በሐኪም ቢሮዎች እና የጤና መምሪያ ውስጥ መገኘት ይችላሉ።
    - ስለ ፍሉ/flu ክትባት - የት መገኘት እንደሚችል በ[‘CDC’ ድህረ-ገጽ] ላይ የበለጠ-መረጃን ማግኘት ይቻላል።

ልጃችሁ ጤናማ ሆኖ መቆየት-እንዲችል እና ሌሎች-እንዳይታመሙ በመከላከል እርዳታ-እንድታደርጉ፤ እናበረታታችኋለን። ስለልጅዎ የጤና ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባክዎን - የልጅዎ የጤና እንክብካቤ ሰጪን  አነጋግሩን።

ጤናማ-የሆነ የበዓል-ወቅት - ለሁላችሁም እንዲሆንላችሁ እንመኛለን!

## የዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ (Summary)



በዲሴምበር (Dec.) 15 ቀን 2022 የትምህርት ቤት ቦርዱ ባደረገው ስብሰባው ላይ፣ በ‘ESSER III funds’ን በመጠቀም ላይ - የ’public hearing’ን አካሂዷል። በተጨማሪም፤ የቅድመ ልጅነት ማዕከል (Early Childhood Center) - “Simply the Best” የሚለውን ፕሬዘንቴሽን ያቀረበ፣ እና የስብሰባው አጀንዳ ያካተተው - የደህንነት-ጥበቃ የዳሰሳ-ጥናትን እና የ ‘SLEP focus group’ የአስተያየቶች ውጤቶች፣ የፖሊሲ መልሶ-ምልከታዎችን እና የFY2024-33 የካፒታል ማሻሻያ ፕሮግራም (Capital Improvement Programs (CIP) በጀትን መቀበልን ያካተተ ነበር።

በዚህ ስብሰባው ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርዱ - ስለ የትምህርት ቤት ቦርድ አባል ታሚ ኢግናቺኦ (Tammy Ignacio) [በ2022-23 ACPS ዋናው-ትኩረት ከሚያደርግባቸው ዙሪያዎችን አንዱ ስለሆነው፣ ስለ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት መማር መልሶ-ማቋቋሚያ (social, emotional and academic learning recovery (SEAL)፣ ላይ ውይይት-ያደረጉበትን] አዲስ ቪዲዮን የሚያሳየውን አጋርቷል። ይህ ቪዲዮ፣ በቅርብ-ጊዜ ያለውን የ‘School Board vignettes’ ተከታታይ-ክፍልን - ስለ ሠራተኞች፣

ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች እና ማህበረሰብ አባላቶች - ከትምህርት ቤት ቦርድ ስራዎቹ - ከውስጣዊ ምልከታዎች ጋር፣ ክፍሉ/division በዓላማው፣ ራዕዩ እና ግቦቹ ላይ ያለውን - ለሕይወት ያለውን የስልታዊ ዕቅድ ጋር እንዴት እንደሚሰራ የሚያሳይ-ነው። ከዚህ-ቀደም የነበሩ በዚህ-ተከታታይ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙት - የሚያካትተው:

- የኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 ቪዲዮ ያቀረበው - የትምህርት ቤት ቦርድ አባል ኬሊ ካርማይክል ቡዝ (Kelly Carmichael Booz) የACPS 2025: Equity for All Strategic Plan's ስልታዊ ግቦን በዘዴያዊ አቀማመጥ ላይ የሚወያየው - አቅርቧል።
- የኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 ቪዲዮ-የሚያሳየው፣ የትምህርት ቤት ቦርድ አባል፣ አብደል-ራህማን ኤልኖቢ (Abdel-Rahman Elnoubi) - ወደ በጀት-ሂደቱ ውስጥ ወደውስጥ-ዘልቆ በማሳየት የሚያቀርበውን አሳይቷል።
- የሴፕቴምበር (Sept.) 22 ቀን 2022 ቪዲዮ የሚያሳየው፤ የትምህርት ቤት ቦርድ ሊቀ-መንበር - ሜጋን አልደርተን (Meagan L. Alderton) - የስልታዊ ዕቅድ (strategic plan)ን በአጠቃላይ ራዕይ፣ ዓላማ፣ እና ዋና እሴቶች የሚያሳየውን የሚያጋራ-ሲሆን፣ እና እንዴት - ከውስጣዊ-ልቡ ጋር ያለውን ከዘር-እኩልነት ጋር የሚገኘው - የ'Equity for All 2025 Strategic Plan' ሊለወጥ-እንደሚችል አሳይቷል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘትም ትችላላችሁ።

## በዲሴምበር (Dec.) 8 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ዲሴምበር (Dec.) 8 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 144.3 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በዲሴምበር (Dec.) 8 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።